ድኅነት

በመጽሐፍ ቅዱስ መዳን ተብለው የተገለጹ የተለያዩ ነገሮችን እናገኛለን። ከእነዚህም ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል።

• ኖኅና ቤተሰቦቹ በመርከብ አማካይነት ከጥፋት ውኃ መዳናቸው፣
• እስራኤላውያን ከግብፅ ባርነት ነጻ መውጣታቸው እና በባሕር መካከል በደረቅ መሻገራቸውና ሲከተሏቸው ከነበሩት ጠላቶቻቸው እጅ መዳናቸ፣
• ንዕማን ሶርያዊ ከነበረበት ለምጽ በዮርዳኖስ ውኃ ታጥቦ መዳኑ፣
• እስራኤላውያን በንጉሡ በሕዝቅያስ ዘመን ከሰናክሬም እጅ በተአምራት መዳናቸው፣

ሆኖም እነዚህ ሁሉ መዳኖች (ድኅነቶች) ለጊዜው ድኅነቱ የተደረገላቸውን ሰዎች ያስደሰቱና ከመከራ ያዳኑ ነገሮች ቢሆኑም ሁሉም ጊዜያዊና ድኅነታቸው በሥጋና በዚህ ዓለም የተወሰነ ነበር። ይህም ማለት የሰውን ልጅ መሠረታዊ ችግር ያልፈታ፣ ሰውን ከተፈረደበት የሞት ፍርድ ያላዳነ፣ በሰው ልጅ የተጎሳቆለ ሕይወት ላይ ይህ ነው የሚባል መሠረታዊና ተጨባጭ ለውጥ ያላመጣ ነበር። ነገር ግን እነዚያ የማዳን ድርጊቶች እግዚአብሔር በልጁ ሰው መሆንና መገለጥ በጊዜው ጊዜ ይፈጽመው

ዘንድ ያለውን አማናዊ ድኅነት በጥላነት (በምሳሌነት) የሚያመለክቱ የተስፋ ጭላንጭሎች ነበሩ።

ድኅነት ማለት ምን ማለት ነው?

ድኅነት ስንል በኃጢአት ምክንያት የወደቀውና የጎሰቆለው የሰው ልጅ ከደረሰበት ድቀትና ሞት ሙሉ በሙሉ ነፃ መውጣቱንና አጥቶት የነበረውን ጸጋ ማግኘቱን፣ መጀመሪያ ከመበደሉ በፊት ወደ ነበረበት ሁኔታ (ከዚያም ወደ በለጠ ደረጃ) መመለሱን ማለታችን ነው። የመዳን ትምህርት (ነገረ ድኅነት) የቤተ ክርስቲያን ትምህርት መሠረትና የመዓዝን ድንጋይ ነው። ማንኛውም አስተምህሮና ሐሳብ የሚመዘነውና የሚለካው በነገረ ድኅነት መሠረት ነው። ከነገረ ድኅነት ጋር የሚጋጭና የሚቃረን ትምህርት ሁሉ ፈጽሞ ተቀባይነት የለውም። የአንድ ትምህርት ወይም አስተሳሰብ ይዘትና አካሄድ ሲተነተን የሰውን መዳን ከንቱ ወደሚያደርግና “የሰው ልጅ አልዳነም” ወደሚል አቅጣጫ የሚወስድ ከሆነ የተለየና የተወገዘ ነው። ስለሆነም ከሐዋርያት ጀምሮ ከዚያ በኋላ የተነሡ ቅዱሳን ሊቃውንት የመናፍቃንን አስተሳሰብና ትምህርት ሲመዝኑና ከንቱነቱንና ስህተትነቱን ሲያጋልጡ የኖሩት በነገረ ድኅነት ማንጠሪያነትና መመዘኛነት እያጣሩና እየመዘኑ ነበር።

“የሰው ልጅ ዳነ” ስንል በአጠቃላይ የሚከተሉትን ያካትታል።

1. ተፈርዶበት የነበረው የሞት ፍርድ ተወገደለት፣ ተነሥቶት (ተወስዶበት) የነበረው ሕይወት ተመለሰለት ማለታችን ነው።

የሰው ልጅ "በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ" ተብሎ አስቀድሞ ተነግሮት የነበረው የሞት ማስጠንቀቂያ በገቢር ተፈጽሞበት፣ በሰውነቱ ላይ ሞት ነግሦበት የሞት ተገዢ ሆኖ ነበር። ዘፍ. 2:17 በሕይወተ ሥጋ እያለም ኑሮው በጽላሎተ ሞት (በሞት ጥላ ሥር) ውስጥ የወደቀና በሞት በፍርሃት የታጠረ፣ ሲሞትም ነፍሱ በጻዕር ተለይታ ሥጋው ወደ መቃብር ነፍሱ ወደ ሲዖል በመውረድ በጭንቅና በመከራ ይኖር ነበር። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞት የሚስማማውን የእኛን ሥጋ በመዋሐድ ሞታችንን ሞቶ በሞቱ ሞትን አጠፋልን፣ የእርሱን ሕይወት ለእኛ ሰጠን፣ ሞትን በትንሣኤ ለወጠልን፣ የመቃብርን ይዞ የማስቀረትና ሰውነታችንን የማፍረስና የመለወጥ ኃይል ድል በማድረግ በመቃብር ተይዞ ፈርሶ በስብሶ መቅረትን አጠፋልን።

በብሉይ ኪዳን የነበሩ ወገኖቻችን የሚኖሩት በሞት ፍርሃት ነበር። ሲሞቱም በጻዕርና በመከራ ነበር። ነቢዩ ዳዊት ይህን በዚያን ዘመን የነበረውን ፍርሃተ ሞት ሲገልጽ እንዲህ ይላል፡-

"ወደንገጸኒ ልብየ በላዕሌየ ወመጽአኒ ድንጋፄ ሞት ፍርሃት ወረዓድ አኃዘኒ ወደፈነኒ ጽልመት ወእቤ መኑ ይሁበኒ ክንፈ ከመ ርግብ እስርር ወአእርፍ - ልቤ በላዬ ተናወጠብኝ፣ የሞት ድንጋጤም ወደቀብኝ፣ ፍርሃትና እንቅጥቅጥ መጡብኝ፣ ጨለማም ሸፈነኝ፣ በርሬ ዐርፍ ዘንድ እንደ ርግብ ክንፍን ማን በሰጠኝ?" መዝ. 54:4-7።

ልበ አምላክ የተባለ ዳዊት በመዝሙሩ እንዲህ አድርጎ የገለጸው በዘመነ ኦሪት ሰው ሁሉ ሞትን ከመፍራቱ የተነሣ ፍርሃተ ሞት ሲያስጨንቀውና ልቡ ሲደነግጥበት የነበረ መሆኑንና ከዚያም የተነሣ ከሞት ፊት ለመደበቅ "በርሬ ዐርፍ ዘንድ ክንፍን ማን በሰጠኝ?" እስከ ማለት ድረስ መሄጃ ያጣና የተጨነቀ የነበረ መሆኑን ነው። ይህን የሰውን ልጅ ሲያስፈራና ሲያስደነግጥ የኖረውን ሞት ከሥሩ ነቅሎ ያጠፋልንና ያስወግድልን ዘንድ ክብር ምስጋና ለዘለዓለሙ ለእርሱ ይሁንና ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆነልን። ሐዋርያው ". . . እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር፣ ይኸውም ዲያብሎስ ነው፣ በሕይወታቸውም ሁሉ ስለ ሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነፃ እንዲያወጣ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ" አለ። ዕብ. 2:14-15

ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ የቃልን ሥጋ መሆን በተናገረበት ድርሳኑ ስለዚህ ሲናገር እንዲህ አለ፡-

“በመሞት ካልሆነ በቀር የሰው ሞት ሊወገድ እንደማይችል እግዚአብሔር ቃል ባየ ጊዜ እርሱ በባሕርዩ የማይሞት ስለ ሆነ ስለ ሁሉም መሞት ይችል ዘንድ የሚሞት የእኛን ባሕርይ ተዋሐደ። የእኛ ባሕርይ ከተዋሐደው ቃል የተነሣ የማይሞት ይሆን ዘንድ፣ መፍረስና መበስበስም በትሣኤ ይጠፋ ዘንድ። የነሣውን ሥጋ ከበደል ንጹሕ የሆነ መሥዋዕት አድርጎ በማቅረብና ለሞት በመስጠት ሞትን ከወገኖቹ አስወገደ። የሞትን ዕዳ ሞትን በመክፈል ከእኛ አስወገደው። ሞትና ጥፋት የእኛን ሥጋ ከተዋሐደው ከአካላዊ ቃል የተነሣ እኛን ሊገዛና ሊይዝ አልተቻለውም። የሁሉ ጌታና መድኃኒት መጥቶ ሞትን ድል ባያደርገው ኖሮ የሰው ዘር ጠፊ ነበር።”

ስለሆነም ክርስቶስ በሞቱ ድል ካደረገው ወዲህ ሞት ኃይሉን ያጣ ደካማ፣ የቀድሞ አስፈሪነቱ ቀርቶ በክርስቲያኖች ዘንድ መሳለቂያና ወደ ማያልፈው ዓለም መሄጃ መንገድ ሆኗል። በዘመነ ክርስትና ሞት ጥፍሩ እንደ ወለቀ፣ ጥርሱ እንደረገፈና ኃይሉ እንደ ደከመ፣ ከዚህም የተነሣ የሕፃናት መጫወቻ እንደ ሆነ አንበሳ፤ እንዲሁም መርዙ እንደ ወጣና ምንም ጉዳት ማድረስ እንደማይችል እባብ ሆኗል።

ሞት በሰው (በአዳም) በኩል መጥቶ በሰው ላይ እንደ ነገሠ በዚሁ መንገድ ሰው በሆነ የእግዚአብሔር ቃል

ሞት ተወገደ። ትንሣኤ ሕይወት ተገኘ። ቅዱስ ጳውሎስ “ሞት በሰው በኩል ስለመጣ ትንሣኤ ሙታን በሰው በኩል ሆኗልና። ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና” እንዳለ። 1 ቆሮ. 15:21-22

አሁን ሰው የሚሞተው “አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ” (ዘፍ. 3:20) በሚለው በቀደመው ፍርድ ሳይሆን ለትንሣኤ ነው። ከአሁን በኋላ እንደ ቀድሞው ለኩነኔ አንሞትም፤ ነገር ግን ከሞት ተነሥቶ የሁሉን ትንሣኤ እንደሚጠብቅ ሰው በራሱ ጊዜ የሚያደርገውን ትንሣኤ ዘጉባኤን እንጠብቃለን። 1 ጢሞ. 6:15

ሐዋርያው “ነገር ግን ሰው፡- ሙታን እንዴት ይነሣሉ? በምንስ ዓይነት አካል ይመጣሉ? የሚል ይኖር ይሆናል። አንተ ሞኝ፣ አንተ የምትዘራው ካልሞተ ሕያው አይሆንም” በማለት ዘር ካልተዘና በአፈር ውስጥ ካልሞተ ሕያው ሆኖ ለመብቀልና ለማፍራት እንደማይችል ሁሉ የሰው ሞትም እንዲሁ በሐዲስ ሰውነት ለመነሣት መሆኑን አስረዳ። 1 ቆሮ. 15:35-36 መቃብርም ለዘለዓለም በዚያው ውስጥ ይዞ የሚያስቀረን ሳይሆን እስከ ትንሣኤ ድረስ የምንቆይበትና ከዚያም የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን፣ የሚሞተው የማይሞተውን ለብሶ የሚነሣበት ነው። በዚያን ጊዜም በኃጢአት ምክንያት ከሰው ተፈጥሮ በኋላ የመጣው “የኋለኛው ጠላት” -

"ሞት" - ድል ይነሣል። 1 ቆሮ. 15:26 እሳት የሚኖረው የሚቃጠል ነገር እስካለ ድረስ ብቻ እንደ ሆነ ሁሉ ሞትም ከትንሣኤ በኋላ የሚሞት ሰውነት ስለማይኖር ራሱ "ይሞታል"፤ ለዘለዓለም ይጠፋል። ይህን ነው ሐዋርያው በመልእክቱ እንዲህ በማለት የገለጸው፡-

"... ሙታንም የማይበሰብሱ ሆነው ይነሣሉ፣ እኛም እንለወጣለን። ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሊለብስ፣ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋልና። ዳሩ ግን ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሲለብስ፣ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሲለብስ በዚያን ጊዜ፡- ሞት ድል በመነሣት ተዋጠ ተብሎ የተጻፈው ቃል ይፈጸማል።" 1 ቆሮ. 15:51-55

2. ወደ እግዚአብሔርና ቅዱሳን አንድነት ተመለሰ፣ ሰላምን አገኘ

ሰው ከእግዚአብሔር አንድነት ተለይቶ የተስፋ ቦታውን አጥቶ ከዓለመ መላእክት ወደ ዓለመ እንስሳት ተጥሎ ነበር። ክብር ምስጋና ይግባውና አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ በተለየ አካሉ ሰው ሆኖ ሰው ወደ ወደቀበት ወደዚህ ዓለም በመምጣትና በእንስሳት በረት በመወለድ የሰውን ልጅ ወደ ራሱ ኅብረትና አንድነት መለሰው። በዚህም መላእክት ከሰዎች ጋር በአንድነት፡-

"ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ - ክብር ለእግዚአብሔር በሰማያት ይሁን፣ ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ" በማለት ሰው ወደ እግዚአብሔር በመመለሱ ደስታቸውን ገለጹ። ሉቃ. 2:14

በመስቀሉ ቤዛነትም በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የነበረው የጠብ ግድግዳ ፈረሰ። ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ክርስቲያኖች በላከው መልእክቱ ይህን እንዲህ ሲል ገልጾታል፡-

"ሁለቱን ያዋሐደ፣ በአዋጅ የተነገሩትንም የትእዛዛትን ሕግ ሽሮ በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳ በሥጋው ያፈረሰ እርሱ ሰላማችን ነውና። .... ይህም ከሁለታቸው አንድ አዲስን ሰው በራሱ ይፈጥር ዘንድ፣ ሰላምንም ያደርግ ዘንድ፣ ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነው። መጥቶም ርቃችሁ ለነበራችሁ ለእናንተ ሰላምን፣ ቀርበው ለነበሩትም ሰላምን የምሥራች ብሎ ሰበከ፤ በእርሱ ሥራ ሁላችን በአንድ መንፈስ ወደ አብ መግባት አለንና።" ኤፌ. 2:14-18

ክርስቶስ ሰላማችን ብቻ አይደለም፤ ይህን ሰላም ራሱን መሥዋዕት አድርጎ በመስጠት አመጣ እንጂ። ሰው ከፈጣሪው ጋር ከተጣላበት ጊዜ ጀምሮ ሐዘን የከበበውና

የተቅበዘበዘ ነበር። ነቢዩ በትንቢት “ሜጥከ ላሕየ ወአስተፍሣሕከኒ ሠጠጥከ ሠቅየ ወሐሤተ አቅነትከኒ - ልቅሶዬን በደስታ ለወጥክልኝ፣ ማቄን ቀደድህ፣ ደስታንም አስታጠቅኸኝ” ብሎ እንደ ተናገረ ሐዘኑን አስወግዶ ደስታን ሰጠው። መዝ. 29:10። መድኃኒታችን “ሰላሜን እተውላችኋለሁ፤ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ” አለ። ዮሐ. 14:27። ይህንም በመስቀሉ ላይ ባደረገው መሥዋዕትነት አረጋገጠ።

በዚህም ከቅዱሳን አንድነት ደመረን። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ክርስቶስ በመስቀሉ ቤዛነት ጥልን ማስወገዱንና ሰላምን ማድረጉን ከገለጸ በኋላ የዚህን ተከታይ ውጤት ሲናገር እንዲህ አለ፡- “እምይእዜሰ ኢኮንክሙ ነግደ ወፈላሴ አላ አንትሙ ሰብአ ሀገሪቶሙ ለቅዱሳን ወሰብአ ቤቱ ለእግዚአብሔር - እንግዲያስ ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮች እና የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም።” ኤፌ. 2:19። እንዲሁም በዕብራውያን መልእክቱ ይህንኑ በተመለከተ ማለትም የሰውን ወደ ቅዱሳን አንድነት መመለስ ሲናገር እንዲህ አለ፡-

“ወደ ጽዮን ተራራና ወደ ሕያው እግዚአብሔር ተራራ ደርሳችኋል፣ ወደ ሰማያዊቱም ኢየሩሳሌም፣ በደስታም ወደ ተሰበሰቡት ወደ አእላፋት መላእክት፣ በሰማያትም ወደ ተጻፉ ወደ በኵራት ማኅበር፣ የሁሉም ዳኛ ወደ ሆነ ወደ እግዚአብሔር፣ ፍጹማንም ወደ ሆኑት ወደ ጻድቃን መንፈሶች፣ የአዲስ ኪዳንም መካከለኛ ወደሚሆን ወደ ኢየሱስ ... ደርሳችኋል።” ዕብ. 12:22-24

ጌታችንም ሰው አስቀድሞ በመብል ምክንያት ከእርሱ ተለይቶ ነበርና በፍጹም ቸርነቱና ፍቅሩ ራሱን መብልና መጠጥ አድርጎ በመስጠት “ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል፤ እኔም በእርሱ እኖራለሁ” (ዮሐ. 6:57) በማለት በራሱ መሥዋዕትነት ከእርሱ ጋር ፍጹም አንድነትን ሰጠን። ከእርሱ ጋር አንድ የምንሆንበትን የቤዛነት ሥራ በመስቀል ላይ ከፈጸመ በኋላ ይህ እስከ ዕለተ ምጽዓት ድረስ በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አማካይነት እንዲቀጥል አደረገ።

3. ልጅነቱ ተመለሰለት

የጸጋ ልጅነቱንና ክብሩን አጥቶ በባርነት ውስጥ ሆኖና ተዋርዶ ለነበረው የሰው ልጅ ዳግመኛ ከእግዚአብሔር የሚወለድበትንና ልጅነትን የሚያገኝበትን ጥምቀትን ሰጠው። ይህ የልጅነት ጸጋም ለሌሎች ከእግዚአብሔር ለሚገኙ ጸጋዎች ሁሉ መሠረት ነው። ልጅ ከሆነ ዘንድ የአባቱን ንብረት ለመውረስ ይችላልና። ይህንም የአባትና የልጅነት ግንኙነት በውስጡ የሚያድርበት መንፈስ ቅዱስ እንዲመሰክርለት አደረገ። “የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር

ይመሰክራል" እንዳለ። ሮሜ. 8:16 እንዲሁም ይኸው ሐዋርያ፡- "ልጆችም ስለ ሆናችሁ እግዚአብሔር አባ አባት ብሎ የሚጮኽ የልጁን መንፈስ በልባችሁ ውስጥ ላከ። ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ ልጅ ነህ እንጂ ባሪያ አይደለህም፤ ልጅም ከሆንህ ደግሞ በክርስቶስ የእግዚአብሔር ወራሽ ነህ።" ገላ. 4:6 ከእንግዲህ የባርነት መንፈስ ሳይሆን "አባ አባት" ብለን የምንጠራበትን የልጅነት መንፈስ ሰጠን። ሮሜ. 8:15

እርሱም "ከእንግዲህ ወዲህ ባሮች አልላችሁም፤ ባሪያ ጌታው የሚያደርገውን አያውቅምና፣ ወዳጆች ግን ብያችኋለሁ፤ ከአባቴ የሰማሁትን ሁሉ ለእናንተ አስታውቄአችኋለሁና" በማለት በኃጢአት በተፈጠረ የጠብ ግድግዳ ምክንያት ከምሥጢሩ ርቀን ከአንድነቱ ተለይተን በባርነት እንኖር የነበረውን ሁኔታ አስወግዶ የዕርቅና የልጅነት መገለጫ የሆኑትን ፈቃዱን ማወቅንና ከባርነት ነፃ መውጣትን ሰጠን። ዮሐ. 15:15 "የፈቃዱን ምሥጢር አስታውቆናልና" ያለው ለዚህ ነው። ኤፌ. 1:9

4. በኃጢአትና በፍትወታት እኩያት ላይ የመቋቋምና የማሸነፍ ኃይልና ሥልጣን አገኘ

ሰው በበደለና ከእግዚአብሔር በተለየ ጊዜ በሰውነቱ ላይ እንደ አረም በቅለው ሠልጥነውበትና ድል አድርገውት ያስጨንቁትና ይገዙት በነበሩ እኩያት ሕሊናትና ፍትወታት ላይ ሙሉ ኃይል አገኘ። ለኃጢአት ባሪያ ሆኖ መገዛቱ ቀርቶ ኃጢአትን የሚያሸንፍበት ኃይል አገኘ። ቅዱስ ጳውሎስ፡- "ከእንግዲህስ ወዲያ ለኃጢአት እንዳንገዛ የኃጢአት ሥጋ ይሻር ዘንድ አሮጌው ሰዋችን ከእርሱ ጋር እንደ ተሰቀለ እናውቃለን" በማለት የገለጸው ይህን ነው። እንዲሁም "አሁን ግን ከኃጢአት አርነት ወጥታችሁ ለእግዚአብሔር ተገዝታችሁ ልትቀደሱ ፍሬ አላችሁ" አለ። ሮሜ. 6:6 ፣ 20-22 ፣ 7:4-6

5. ፈጣሪውን እንዲያውቅ ተደረገ

እግዚአብሔር ሰውን በመልኩና በአርአያው የፈጠረው ሩቅ ያልሆነና በእርሱ ዘንድ ያለ የፈጣሪውን አርአያ እያሰበና እየተመለከተ በፍቅሩ ሆኖ በተዘክሮው ጸንቶ እንዲኖር ነበር። ሰው ግን የተደረገለትን ታላቅ ነገር ረስቶ በጸጋው መጠቀምን ትቶ በአርአያውና በመልኩ የፈጠረውን እግዚአብሔርን ረሳ፤ መርሳት ብቻም ሳይሆን ያገለግሉትና ይጠቀምባቸው ዘንድ የተፈጠሩለትን ከእርሱ በታች ያሉትን የተለያዩ ፍጥረታትንና የእጅ ሥራዎችን አመለከ። በፈጣሪ ፋንታ ለፍጡር ተንበረከከ፤ ከዚህም በላይ የእግዚአብሔርን ክብር ለዕቃውና ለድንጋዩ፤ ለቁሳቁሱ ሁሉ ሳይቀር ሰጠ፤ ከዚህም ወደ ባሰ ሄዶ አጋንንትንም እስከ ማምለክ ደረሰ። በጨለማ የተቀመጠ ሰው አገኝ አጣውን እንደሚዳስስ እንዲሁ ሳይመርጥ ያገኘውን ሁሉ የሚያመልክ ሆነ። ሮሜ 1:9-25 እርሱ ሊገዛቸውና ሊያገለግሉት፣ እንዲሁም የፈጣሪውን ህልውናና ሥራ ለማወቅ እንዲረዱት

ለአንክሮና ለተዘክሮ የተፈጠሩለትን ፍጥረታት አመለካቸው።
ነቢዩ ይህን በተመለከተ በማዘንና በመገረም እንዲህ ይላል፡-
“የዝግባን፣ የዞጲንን፣ የኮምቦልንና የጥድን ዛፍ ይተክላል፣ ዝናብም ያበቅለዋል። ለሰውም ማገዶ ይሆናል፤ ከእርሱም ወስዶ ይሞቃል፣ አንድዶም እንጀራ ይጋግርበታል፤ ከእርሱም አምላክ አበጅቶ ይሰግድለታል፣ የተቀረጸውንም ምስል ሠርቶ በእርሱ ፊት ይንበረከካል። ግማሹን በእሳት ያቃጥላል፣ ሥጋም ይጠብስበትና ይበላል . . . የቀረውንም እንጨት አምላክ አድርጎ ምስል ይቀርጽበታል፤ በፊቱም ተጎንብሶ ይሰግዳል፣ ወደ እርሱም እየጸለየ፡- አምላክ ነህና አድነኝ ይላል።” ኢሳ. 44:12-17

ሰው ሥነ ፍጥረትን እንዲያ ሲያመልክ በአንጻሩ ግን የራሱን አስገኚና ሥነ ፈጥረትን ሁሉ የፈጠረውን እግዚአብሔርን ረሳው። በእግዚአብሔር አርአያ የመፈጠር ጸጋ በራሱ ሰው እግዚአብሔርን እንዲያውቅ ያስችለው የነበረ ቢሆንም ሰው ግን በዚህ ፈጣሪውን ማወቅ ባለመቻሉ በሥነ ፍጥረት ያውቅ ዘንድ ሥነ ፍጥረትን ሰጠው። ወደ ሰማይ ተመልክቶ የሥነ ፈጥረትን ስምምነትና ሥርዓት ተረድቶ ፈጣሪውን ማወቅ ይችል ነበር። በዚህም ባይችል ሕግ በመስጠት፣ ነቢያትን በመላክ ሌላ ዕድል ሰጠ። ሰው ግን በጊዜያዊ ተድላ ደስታና በአጋንንት ምትሐት በመታለል ራሱን ወደ እውነት መምራት አልቻለም።

ሰው እንዲህ ፈጣሪውን አውቆ እንዲኖር ለክብር ተፈጥሮ ሳለ ነገር ግን ከእርሱ በታች ያሉትን እስከ ማምለክ ድረስ ተዋርዶ ፈጣሪውን ማወቅ ተስኖት እንዲቀር እግዚአብሔር አልፈቀደም። ይህም ከቸርነቱ የተነሣ ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል ሰው በመሆን ሰውን እርሱን እንዲያውቀው አደረገ። ሰው ሆኖም “ሰው እንደ ገና ካልተወለደ” አለ። ዮሐ. 3:3። ይህም ለሁለተኛ ጊዜ የሚሆን ልደተ ሥጋ ሳይሆን ነፍስ በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል እንደ ገና ካልተወለደችና ካልታደሰች ማለቱ ነው። ሰዎች አወቅን፣ ተጠበብን እያሉ ነገር ግን የጥበብ መጀመሪያ የሆነውን ፈጣሪያቸውን ማወቅ ስላልቻሉ፣ የሰው ጥበብና ዕውቀት ሰፊ ጊዜ ተሰጥቶ ተፈትኖ ስለ ወደቀ አምላክ በሚታይ ሥጋ በመገለጥ ራሱን ለሰው ገለጠ። 1 ጢሞ. 3:16 ሐዋርያው “ዓለም በጥበብዋ እግዚአብሔርን ስላላወቀች በስብከት በሞኝነት የሚያምኑትን ሊያድን የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ሆኗልና” እንዳለ። 1 ቆሮ. 1:21

ቅዱስ አትናቴዎስ ስለዚህ ጉዳይ የቃልን ሥጋ መሆን (በእንተ ተሠግዎተ ቃል) በተናገረበት ድርሳኑ ሰፋ አድርጎ በመተንተን እንዲህ ይላል፡-
“ሰዎች እግዚአብሔርን ማሰብ ትተው ለራሳቸው

መዋትያን ሰዎችንና አጋንንትን አምላክ አድርገው ማምለካቸውን ባየ ጊዜ ሰውን ወዳጅ የሆነ የዓለም መድኃኒት እግዚአብሔር ወልድ ሥጋን ተዋሐደ፣ እንደ ሰውም በመመላለስ ሰው እርሱን ወደ ማወቅ እንዲመለስ አደረገ። ፍጥረትን በመፍራት ፍጥረታትን አምላክ ብለው እስኪያመልኩ ከደረሱ. የፍጥረቱ ባለቤት ሰው ሆኖ ሲመጣ ያምኑ ዘንድ፣ ሕሊናቸው ወደ ሰዎች አዘንብሎ አማልክት ናቸው እስከ ማለት ከደረሱ የእርሱን ሥራውን አይተውና ሌሎች ፍጡራን ካደረጉት ጋር አነጻጽረው ከዚያ በፊት እንደ አማልክት ያከብሯቸው ለነበሩት ሁሉ ጌታቸውና ፈጣሪያቸው መሆኑን አውቀው አምልኮታቸውን ወደ እርሱ እንዲመልሱ፣ ርኩሳን መናፍስትን ወደ መፍራት፣ ማመንና ማምለክ ያዘነበሉትንም እነዚያን ክርስቶስ ሲያባርራቸውና ሲያስወጣቸው አይተው እርሱ ብቻ አምላክ እንደ ሆነና ርኩሳን መናፍስት ግን ምንም አለመሆናቸውን እንዲረዱ ነው።

“የሞቱ ሰዎችን (ሙታንን) እንደ ጀግናና እንደ አማልክት የሚያከብሩና የሚያመልኩም ቢሆኑ የጌታን ትንሣኤ አይተው የእነዚያን ሐሰትነትና ጌታችን የፍጡራን ብቻ ሳይሆን የሞት እንኳ ጌታ መሆኑንና ብቸኛው አምላክ እርሱ መሆኑን ያውቁ ዘንድ። ስለዚህ ምክንያት ጌታችን ሰው በመሆን ተገለጸ፣ የሰዎችን ሥራ ኢምንት የሚያደርግ ሥራ ሠራ፣ ሰውን በማንኛውም መንገድ

የሚያደርግ ሥራ ሠራ፣ ሰውን በማንኛውም መንገድ
ቢስት ይመልሰውና ያድነው ዘንድ፣ እውነተኛ አምላክ እርሱ ብቻ መሆኑን ያሳወቀው ዘንድ። ይህም አምላክ ሰው የሆነበት ሁለተኛው ምክንያት ነው።”

በአጠቃላይ እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው በመለኮታዊ ጸጋው አስቦለትና አዘጋጅቶለት የነበረውና በመካከል በገባ ኃጢአት ምክንያት አጥቶት የነበረው ነገር ሁሉ ተመለሰለት፣ በኃጢአት ምክንያት የመጡ ነገሮች ሁሉ ተወገዱ። 2 ቆሮ. 5:18-19 ፣ ቆላ. 1:19-24 ፣ ሮሜ. 8:1-4 ፣ 2 ቆሮ. 3:18

ሰው የዳነው እንዴት ነው?

መዳናችን (ድኅነታችን) የተገኘው በእኛ ሥራ መልካምነት አይደለም። እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ከሞት ወደ ሕይወት ያሸጋገረው እርሱን የሚያስደስትና እንዲያ እንዲያደርግለት የሚያበቃው የተቀደሰ ሕይወት ስለነበረው አይደለም። በኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮ ሰው የዳነው በእግዚአብሔር ቸርነት (ጸጋ) ነው። የሰው ድኅነት የእግዚአብሔር የቸርነቱ ስጦታና ለሰው ያለው የማይለወጥ ፍቅር ውጤትና መገለጫ ነው። የእኛን የቀደመ ሁኔታና እግዚአብሔር እንዴት እንዳዳነን ሐዋርያው ግልጽ በሆነ ሁኔታ እንዲህ ሲል ያስተምረናል፡-

“እኛ ሁላችን ደግሞ የሥጋችንንና የልቡናችንን ፈቃድ እያደረግን፣ በሥጋችን ምኞት በፊት እንኖር ነበርን። እንደ ሌሎችም ደግሞ ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን። ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለጸጋ ስለሆነ ከወደደን ከታላቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወትን ሰጠን፣ በጸጋ ድናችኋልና። በሚመጡ ዘመናትም በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ባለው ቸርነት ከሁሉ የሚበልጠውን የጸጋውን ባለጠግነት ያሳይ ዘንድ ከእርሱ ጋር አስነሣን፤ በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን።” ኤፌ. 2.3-8።

ሰው ሁሉ በአዳም በደል ምክንያት “የቁጣ ልጅ” ነበር፤ ሁሉም በኃጢአት ምክንያት የሞተ ነበር። ሮሜ 8:10። አሁንም ይኸው ሐዋርያ ስለዚሁ ጉዳይ ሲናገር ለደቀ መዝሙሩ ለቲቶ በላከው መልእክቱ እንዲህ አለ፡- “እኛ ደግሞ አስቀድመን የማናስተውል ነበርንና፤ የማንታዘዝ፤ የምንስት፤ ለምኞትና ለልዩ ልዩ ተድላ እንደ ባሪያዎች የምንገዛ፣ በክፋትና በምቀኝነት የምንኖር፤ የምንጣላ፤ እርስ በርሳችን የምንጠላላ ነበርን። ነገር ግን የመድኃኒታችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ሰውን መውደዱ በተገለጠ ጊዜ እንደ ምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው ጥምቀትና በመንፈስ መታደስ አዳነን እንጂ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለነበረው ሥራ አይደለም።” ቲቶ. 3:3-5።

ጌታችንና መድኃኒታችንም እግዚአብሔር ሰውን የወደደውና ያዳነው እንዲሁ በአባታዊ ፍቅሩ መሆኑን ሲገልጽ፡- “በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን (ሰውን) እንዲሁ ወዷልና” አለ። ዮሐ. 3:16 የወደደን እንዲሁ በቸርነቱ እንጂ እንዲወደን የሚያደርግ መልካም ሥራ ስለነበረን ወይም እኛ ስለ ወደድነው አይደለም። ሰውማ በራሱ ጥፋት ከአምላኩ ፊት የኮበለለ ነበር። ጌታችን በጠፋው በግ ምሳሌ እንደ ተናገረው የጠፋውን አዳምን “የሰውን ልጅ በሙሉ” ይፈልገውና ወደ ቀደመ ክብሩ ይመልሰው

ዘንድ ከሉዐላዊ መንበሩ ወርዶ ፈለገው፤ ባገኘውም ጊዜ ለመፈለግ በደከመው ድካም ሳይቆጣው፣ ሳይገርፈው፣ በእግርህ ሂድ ሳይለው በማግኘቱ ተደስቶ በጫንቃው ላይ ተሸከመው። በጠፋው ልጅ ምሳሌ እንደ ተናገረው ያጠፋውን ጥፋትና የበደለውን በደል ሳያሰብ አዘነለት፣ በፍጹም ፍቅር ተቀበለው፣ የሰባውን በማረድ (የራሱን ቅዱስ ሥጋውን በመቁረስና ክቡር ደሙን በማፍሰስ) በዓል አደረገለት። "ይህ ልጄ ሞቶ ነበርና ደግሞም ሕያው ሆኗል፣ ጠፍቶም ነበር ተገኝቷልም፤ ደስ እንዲለን ፍሥሐም እንድናደርግ ይገባናል" አለ። ሉቃ. 15፡11-32

ቅዱስ ጳውሎስም ይህንኑ ሲገልጽ፡- "እናንተንም ነውርና ነቀፋ የሌላችሁና ቅዱሳን አድርጎ በእርሱ ፊት ያቀርባችሁ ዘንድ፣ በፊት የተለያችሁትን፣ ክፉ ሥራንም በማድረግ በአሳባችሁ ጠላቶች የነበራችሁትን አሁን በሥጋው ሰውነት በሞት በኩል አስታረቃችሁ" አለ። ቆላ. 1፡21-22 ይህን ሁሉ አጠቃልሎ "ወሶበ እንዘ ጸሩ ንሕነ ለእግዚአብሔር ተሣሃለነ በሞተ ወልዱ - እግዚአብሔር ጠላቶቹ ሳለን በልጁ ሞት ታረቀን" አለ። ሮሜ. 5:10 ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም- "እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፣ በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ" በማለት የዳንነው ክርስቶስ በቸርነቱ በተቀበለው ሕማምና መከራ መሆኑን ይነግረናል። 1 ጴጥ 2:24።

ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስም እንዲህ ይላል፡- "በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ፤ በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና። ፍቅርም እንደዚህ ነው፤ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደ ወደደን ስለ ኃጢአታችንም ማስተሥረይ ይሆን ዘንድ ልጁን አንደ ላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደ ወደድነው አይደለም።" 1ዮሐ. 4:9-10

የወደቀውንና የሞተውን የሰው ልጅ ያዳነው የእግዚአብሔር ቸርነት እንጂ የእርሱ ሥራ አይደለም። ሰው በሥራው ብቻ የሚጸድቅ ቢሆን ኖሮ በብሉይ ኪዳን የነበሩ ደጋግ አባቶች ለመዳን ክርስቶስ ባላስፈለጋቸው ነበር። ነገር ግን ምንም እንኳ በደጋግ ሥራቸው በኃጥአን ላይ የሚደርሰው መከራ ሙሉ በሙሉ ባይደርስባቸውም ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ በአዳም በደል ምክንያት የተዘጋችውን ገነት እስኪከፍታት ድረስ ከሲኦል መውጣትና ወደ ገነት መግባት አልቻሉም። በኃጢአት ምክንያት ከመጣው ፍዳ አንዷንም ፈቀቅ ማድረግ አልቻሉም። ስለዚህ እኛን ያዳነን የክርስቶስ ቸርነት እንጂ ሥራችን አይደለም ማለት ነው። እንደ ሥራችንማ ቢሆን እግዚአብሔር ሰው ኾኖ ኃጥአን ለሆንነው ለእኛ መከራ ይቀበል ዘንድ የሚያበቃው የትኛው ሥራችን ነበር? በእኛ ሥራ ቢሆንማ ኖሮ እንኳን ይህ ሁሉ ቸርነት ሊደረግልን ቀርቶ ከተደረገልን ቸርነት

አንዷንም እንኳን ባላገኘን ነበር። የእግዚአብሔር ስጦታ በዋጋ የሚገዛ አይደለም።

በኃጢአት ድካም ሳለን በቸርነቱ የወደደንና ያዳነን መሆኑን በማድነቅ ሐዋርያው እንዲህ ይላል፡-
“ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቷልና። ስለ ጻድቅ የሚሞት በጭንቅ ይገኛልና፤ ስለ ቸር ሰው ግን ሊሞት እንኳ የሚደፍር ምናልባት ይገኝ ይሆናል። ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቷልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል።” ሮሜ. 5:6-9።

ቅዱስ ጳውሎስ በሚገባ እንደ ገለጸው እኛ ጻድቃን ሆነን ክርስቶስ ቢሞትልን ኖሮ ምናልባት ብዙም ላይደንቅ ይችል ይሆናል። ምክንያቱም ለጻድቅ ሰው ተላልፎ የሚሞት ምናልባት ይገኝ ይሆናልና ነው። ነገር ግን ኃጢአተኞች ሳለን ስለ እኛ መሞቱ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍጹም ፍቅርና የቸርነቱን ገናናነት ያስረዳል። ለምሳሌ ለሞት የሚያበቃ ወንጀል ሠርቶ ሞት ለተፈረደበት ኃጢአተኛ ሰው “እኔ እሞትለታለሁ” ብሎ ራሱን አሳልፎ የሚሰጥ ማን ነው? ክርስቶስ ለእኛ ያደረገው ይህንን ነው፤ በኃጢአታችን ሞት የተፈረደብን “የሞት ሰዎች” ሳለን በፍጹም ፍቅሩ ስለ እኛ ራሱን ቤዛ አድርጎ ሰጠ፣ ሞተልን፤ በሞቱም ከሞት አዳነን፣ ሕይወትን ሰጠን። ይህ የእርሱ የጸጋ ስጦታ ብቻ ነው።

ሕይወትን ሰጠን። ይህ የእርሱ የጸጋ ስጦታ ብቻ ነው።
ኢሳ 53:4-6 ይህን ሁሉ ቸርነት ያደረገልን፣ የሞት ሰዎች ሳለን በማይነገር ፍቅሩ ሕይወትን የሰጠን አምላካችን እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን አሜን።

ሰው ለመዳን ምን ያስፈልገዋል?

ሰውን ያዳነው የእግዚአብሔር ጸጋ መሆኑ ተገልጿል። ነገር ግን ይህን መዳን ለመፈጸምና በተሰጠው የመዳን አገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን ከእያንዳንዱ ሰው የሚጠበቅ ነገር አለ። ሐዋርያው የእግዚአብሔርን የማዳን ነገር ሲገልጽ፡- “እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው” በማለት ንጹሐ ባሕርይ የሆነ ክርስቶስ ስለ እኛ ኃጢአት “ኃጥእ” ተብሎ መከራ በመቀበሉ የእኛ ኃጢአት መወገዱንና በእርሱ “ኃጥእ” መባል እኛ “የእግዚአብሔር ጽድቅ” መሆናችንን ገለጸ። በመቀጠልም እንዲህ አለ፡- “አብረንም እየሠራን የእግዚአብሔርን ጸጋ በከንቱ እንዳትቀበሉ ደግሞ እንለምናለን” 2 ቆሮ. 5:21 ፣ 6:1 ይህም ማለት እግዚአብሔር ያደረገልንን የማዳን ጸጋ ለመቀበል ከእኛ የሚጠበቀውን (ምንም እንኳ የምናደርገው ነገር ለጸጋው ምንም የማይመጥንና እዚህ ግባ የሚባል ባይሆንም) ነገር ሳናደርግ እንዳንቀር ነው። ይህም እያንዳንዳችን ማድረግ ያለብን የራሳችን ድርሻ ያለ መሆኑን በግልጽ የሚያስገነዝብ ነው። ከእርሱ የሚጠበቅበትን ለማይፈጽም ሰው የእግዚአብሔር ሰውን ማዳን ብቻ በራሱ ተጠቃሚ አያደርገውም።

አንድ ሰው ለመዳን የሚከተሉትን መፈጸም ይኖርበታል።

1. እግዚአብሔር ሰውን ለማዳን በፈቃዱ ያደረገውን ነገር ሁሉ ማመንና መቀበል (እምነት)፡-
ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ከመወለድ ጀምሮ ለሰው ሲል ያደረውን - መጠመቁን፣ ዞሮ ማስተማሩንና ያስተማረውን ቃልና ትእዛዝ ማመንን፣ መከራ መቀበሉን፣ በመጨረሻም በራሱ ፈቃድ ለእኛ ሲል መሞቱን፣ መቀበሩንና በሦስተኛው ቀን መነሣቱን እና በአርባኛው ቀን ወደ ቀደመ ክብሩ ማረጉን . . . በአጠቃላይ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምታምነውን ሁሉ በፍጹም ልብ ማመን ያስፈልጋል። እግዚአብሔር እኛን ለማዳን ያደረገውን ልዩ ቸርነትና እናምነው ዘንድ የገለጠውን እውነት የማያምን ሰው ሊድን አይችልም።

እግዚአብሔር ያደረገውን ቸርነትና የፈጸመውን ድኅነት ለማያምን ሰው ለእርሱ ልክ የሰው ድኅነት እንዳልተፈጸመና ገና እንዳልዳነ ይሆንበታል። ይህም ማለት በኢየሱስ ክርስቶስ የማያምን ሰው አሁን እየኖረበት ያለው ዘመኑ ዘመነ ወንጌል ዓመተ ምሕረት ቢሆንም እርሱ ግን በዘመነ ኦሪት በዓመተ ፍዳ እንደ ነበሩት ሰዎች ይሆናል ማለት ነው። በእርግጥ እንዲያውም በዚያ ዘመንም ወደፊት በዘመነ ወጌል የሚሆነውን በእምነት አሻግረው ያዩና በተስፋ የጠበቁ ደጋግ አበው ነበሩ። ከዘመኑ ሳይደርሱ እንደ ደረሱ ሆነው ሥጋዌው ከፊታቸው ግልጽ ብሎ እየታያቸው ዕለቱን እንደ

ተፈጸመ እያደረጉ ትንቢት የተናገሩ ነቢያትም ነበሩ። አሁን በዘመነ ወንጌል በዓመተ ምሕረት እየኖረ የማያምን ኢአማኒ ሰው ግን ከዘመነ ብሉይ እንደ ነበሩት አሕዛብ ያለ ነው። ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ በኢየሱስ ክርስቶስ ያላመነን ሰው ምን እንደሚገጥመው ሲናገር፡- "በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም" ያለው ለዚህ ነው። ዮሐ. 3:36

ጌታችን በቅዱስ ቃሉ፡- "እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው፣ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም" በማለት ማመን የሕይወት መንገድ መሆኑን አስተምሯል። ዮሐ. 5:24። እንዲሁም "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር እንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና። ... በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም፤ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል" በማለት በእርሱ ማመን የድኅነት መሠረት ሲሆን አለማመን ደግሞ የፍርድና የሞት መንገድ መሆኑን ግልጽ ባለ ቃል አስረዳ። ዮሐ. 3:18 ፣ ዮሐ. 4:5 ፣ ዮሐ. 5:10

ጌታችን "የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቻቸዋለሁና፤ እነርሱም ተቀበሉት፣ ከአንተም ዘንድ እንደ ወጣሁ በእውነት አወቁ፣ አንተም እንደ ላክኸኝ አመኑ" በማለት እምነት እርሱ የነገረንን ቃል መቀበልና ማመን መሆኑን ተናግሯል። ዮሐ. 17:8 በአጠቃላይ እግዚአብሔር እርሱን ማወቅ በምንችለው መጠን እናውቀውና እናምነው ዘንድ፣ ወደ እውነት ይመራን ዘንድ በቅዱስ መጽሐፍ የገለጠውን እውነት መቀበልና ማመን ለድኅነት የግድ ነው። "ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ፣ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና" እንደ ተባለ። ዕብ. 11:6

ሃይማኖት የድኅነት መሠረት ነው። ቤት ያለ መሠረት ሊቆም እንደማይችልና በአየር ላይ ሕንፃ መገንባት እንደማይቻል ሁሉ የዘለዓለማዊ ድኅነት መሠረትም ሃይማኖት ነው። ለመዳን አንድ አምላክ የሆነውንና በአንድነቱ ውስጥ ልዩ ሦስትነት ያለውን የሕያው ባሕርይ የእግዚአብሔርን ህልውናውን፣ ፈጣነቱን፣ አዳኝነቱን ... ማመን፣ የእግዚአብሔር ወልድን ሥጋዌውን፣ ሞቱን፣ ተዋሕዶውን፣ ትንሣኤውን፣ . . . ማመን ለመዳን ሊታለፉ የማይችሉ ቁልፎች ናቸው። ያለዚህ እምነት ወይም ከዚህ የወጣ እምነት አያድንም።

2. ለድኅነት መሠረታዊ የሆኑ ምሥጢራትን መፈጸም

ከማመን ቀጥሎ ለድኅነት ወሳኝና አስፈላጊ የሆኑ ምሥጢራትን መፈጸም ይገባል። እነዚህም በመጀመሪያ ጥምቀት፤ ሜሮን፤ እና ቁርባን ሲሆኑ ከዚያ በኋላ

በሕይወት ሂደት ለሚገጥሙ ነገሮች ደግሞ ንስሐ ናቸው።

ምሥጢረ ጥምቀት
በጥምቀት ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ጋር እንተባበራለን። ሐዋርያው ይህን እንዲህ በማለት ይገልጸዋል፦ “ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን።” ሮሜ. 6:5-6 ይህም ማለት ከክርስቶስ ሞትና በሞቱ ከተገኘው ሕይወት ጋር የምንተባበረው በጥምቀት አማካይነት ነው። ክርስቶስ ወደ መቃብር ወርዶ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ቆየ እኛም የፈለገ ዮርዳኖስ አምሳል በሆነ ውኃ ውስጥ ሦስት ጊዜ በመግባት ከሞቱ ጋር መተባበራችንን እንመሰክራለን። ከዚያም ክርስቶስ ሞትን በራሱ ኃይል ድል አድርጎ እንደ ተነሣ እኛም ከውኃው በመውጣት ትንሣኤውን እንመሰክራለን። እንዲህ በማድረግም ሞቱን በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር በመተባበር በትንሣኤውም እንተባበራለን፤በማለትም ዘለዓለማዊ ለሆነው የሕይወት ትንሣኤ እድምተኞች እንሆናለን።

ከየሀገሩ በዓለ ሰዊትን ለማክበር በኢየሩሳሌም ተሰብስበው የነበሩ አይሁድ ቅዱስ ጴጥሮስ የዘለዓለም ሕይወትን ይወርሱ ዘንድ ሲያስተምራቸው በትምህርቱ ልባቸው ተነክቶ “ምን እናድርግ?” ብለው ለጠየቁት ጥያቄ ይድኑ ዘንድ መጠመቅ እንዳለባቸው ሲያስረዳቸው “ንስሐ ግቡ፣ ኃጢአታችሁም ይሠረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ . . . ” ነበር ያላቸው። የሐዋ. 2፡38 ይድኑ ዘንድ የሐዋርያትን ትምህርት ሰምተው በጌታ አምላክነት ያመኑ እነ ሊዲያ፣ ቆርኔሌዎስ፣ የወኅኒ ጠባቂው ሁሉ ተጠምቀዋል። የሐዋ. 10፡47 ፣ 16፡15 ፣ 33 ስለዚህ የሰው ልጅ ይድን ዘንድ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ሊጠመቅ ይገባዋል። ማቴ. 28፡19-20

በዚህ ዓይነት ያልተጠመቀ ከክርስቶስ ጋር ኅብረት የለውም። ክርስቶስ በሞቱ ሞትን ድል ማድረጉን አምኖ ይህን እምነቱን (በጥምቀት) ስላልመሰከረና ሞቱን በሚመስል ሞት (ወደ ውኃ ውስጥ በመግባትና በመጠመቅ) ከእርሱ ጋር ስላልተባበረ በትንሣኤው ሊተባበር ማለትም የሕይወት ትንሣኤን ሊያገኝ አይችልም።

ክርስቶስ በሞቱ ሞትን የደመሰሰው መሆኑ ከላይ ተገልጾአል። አስቀድሞ ነቢዩ ኢሳይያስ በትንቢት፦ “ሞትን ለዘለዓለም ይውጣል” በማለት፣ ነቢዩ ሆሴዕም “ሞት ሆይ፣ መውጊያህ የት አለ? ሲኦል ሆይ ማጥፋትህ ወዴት ወዴት አለ?” በማለት የተናገሩት የሞት ድል መነሣት በመድኃኒታችን ከተፈጸመ በኋላ ሐዋርያው ይህንኑ አስታውሶ “ሞት ሆይ፣ መውጊያህ የት አለ?

ሲኦል ሆይ፣ ድል መንሣትህ የት አለ?" በማለት በሞት ላይ የተነገረው ትንቢት መፈጸሙን ገለጸ። ኢሳ. 25:8 ፣ ሆሴ. 13:14 ፣ 1 ቆሮ. 15:55

ይህ የሞት ድል መነሣት ለእያንዳንዳችን የሚደርሰን በእምነት ተመሥርተን ሞቱን በሚመስል ሞት በጥምቀት ውስጥ ስናልፍ ነው። በጥምቀት ከእርሱ ጋር በመተባበር ካልሆነ በስተቀር በሞት ላይ በአዋጅ የተደረገው ሽረትና ድል መንሣት ለማንም ሊደርሰው አይችልም።

ለዚህ ነው በዮሐንስ ወንጌል ላይ እንዲህ የሚለው፡- "ዘየአምን በወልድ ቦ ሕይወት ዘለዓለም ወዘሰ ኢየአምን በወልድ ኢይሬእያ ለሕይወት ዘለዓለም አላ መቅሠፍተ መዓቱ ለእግዚአብሔር ይነብር ላዕሌሁ - በልጁ የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው፤ በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም።" ዮሐ. 3.36።

ለሕይወት የሆነ አዲስ ሰውነትን ገንዘብ የምናደርገውና ክርስቶስን የምንለብሰው በጥምቀት ነው። "የተጠመቃችሁ ሁላችሁ ክርስቶስን ለብሳችኋልና" እንዳለ። ገላ. 3:27 ያልተጠመቀ ሰው ክርስቶስን ሊለብስና አዲስ ተፈጥሮን ገንዘብ ሊያደርግ አይቻለውም። "ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው" ያለው ለዚህ ነው። 1 ቆሮ. 5:17

መድኃኒታችንም "ያመነ የተጠመቀ ይድናል፤ ያላመነ ግን ይፈረድበታል" በማለት ግልጽ በሆነ ሁኔታ ያለ ጥምቀት ድኅነት የሌለ መሆኑን ተናግሯል። ማር 16:16። "ያላመነ ያልተጠመቀ ይፈረድበታል" በማለት ፋንታ "ያላመነ ይፈረድበታል" ያለው ያላመነ ሰው ለመጠመቅ የሚፈልግበት ምክንያት ስለሌለ ነው። ምክንያቱም አንድ ሰው የሚጠመቀው የጥምቀትን ጥቅም ሲረዳና ሲያምን ነው። ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ሐዋርያው ፊልጶስ ያስተማረውን ስላመነ፡- "ነዋ ማየ ወመኑ ይከልአኒ ተጠምቆ - እነሆ ውኃ፤ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድን ነው?" አለው። ፊልጶስም "ይደልወከ ከመ ትእመን በፍጹም ልቡናከ - በፍጹም ልብህ ልታምን ይገባሃል" አለው። እርሱም "አነ አአምን ከመ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልዱ ለእግዚአብሔር - ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ አምናለሁ" በማለት እምነቱን መስክሮ ተጠመቀ። የሐዋ 8:35-38 የማያምን ሰው መጠመቅ አይፈልግም፣ ሊጠመቅም አይገባውም፣ ቢጠመቅም አይጠቅመውም። ይህ እምነት ወሳኝ ስለሆነ ሕፃናት ሲጠመቁ የክርስትና እናት ወይም አባት ስለ እነርሱ ጸሎተ ሃይማኖትን እንዲደግምላቸውና ሲያድጉም ሃይማኖታቸውን እንዲያስተምሯቸው በእግዚአብሔር ፊት አደራ ይቀበላል፣ ቃል ይገባል።

ይህ "ያመነ የተጠመቀ ይድናል፤ ያላመነ ግን ይፈረድበታል" የሚለው ቃለ ወንጌል የሕፃናትን ጥምቀት

የሚከለክል አይደለም። ይልቁንም ጥምቀት ለእነርሱም አስፈላጊ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ምክንያቱም ጥምቀት ለመዳን አስፈላጊ እንደ መሆኑ መጠን እነርሱም ይድኑ ዘንድ ሊጠመቁ ግድ ይላልና። በመሠረቱ ይህ የተነገረው በተለያየ ምክንያት ሳይጠመቁ ላደረጉና ማመን በሚችሉበት ዕድሜ ላይ ለደረሱ ሰዎች ነው እንጂ የሕፃናት ጥምቀትን በተመለከተ የተነገረ አይደለም። ለምሳሌ ቅዱስ ጳውሎስ፡- "ሊሠራ የማይወድ አይብላ" ያለው መሥራት እየቻሉ በስንፍና ምክንያት መሥራት የማይወዱትን እንጂ በዕድሜ ሕፃናት የሆኑትንና በተለያዩ ምክንያቶች መሥራት የማይችሉትን የሚመለከት አለመሆኑ ግልጽ ነው። 2 ተሰ. 3፡10 ያውም "ሊሠራ የማይወድ" አለ እንጂ "የማይሠራ" አላለም። ሳይጠመቅ ቆይቶ ማመን በሚችልበት ዕድሜ የደረሰ ሰው ግን ከመጠመቁ በፊት የክርስትናን ትምህርት በሚገባ ሊማርና ሊያምን ይገባዋል። ከክርስቲያን ቤተሰቦች የተወለዱ ሕፃናት ግን በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት ወንዶች በተወለዱ በአርባ ቀን፣ ሴቶች ደግሞ በሰማንያ ቀናቸው ይጠመቃሉ። ትምህርቱን ደግሞ እያደጉ በሒደት ይማራሉ። ይህ የሕፃናት ጥምቀትም ከጥንት ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ ሲሠራበት የኖረ መጽሐፍ ቅዱሳዊና ትውፊታዊ ነው። የሐዋ. 16፡33 ፤ 1 ቆሮ. 1፡15

ጥምቀት ለድኅነት ወሳኝ መሆኑን ቅዱስ ጴጥሮስም ሲገልጽ፡- "ይህም ውኃ ደግሞ ማለት ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድነናል፣ ይህም የሰውነትን እድፍ ማስወገድ አይደለም" አለ። 1 ጴጥ. 3፡21 ይኸው ሐዋርያ በበዓለ ሃምሳ ያመኑት ሦስት ሺህ ሰዎች "ምን እናድርግ?" ባሉ ጊዜ "ንስሐ ግቡ፤ ኃጢአታችሁም ይሠረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ" ያላቸው በጥምቀት ሥርየት ኃጢአትና ድኅነት የሚገኝ በመሆኑ ነው። በሁለተኛው ዓለም አቀፋዊ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ በ381 ዓ.ም. በቁስጥንጥንያ የተሰበሰቡት ቅዱሳን አባቶችም በጸሎተ ሃይማኖት ላይ፡- "ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት ለሥርየተ ኃጢአት - ኃጢአት በሚሠረይባት በአንዲት ጥምቀት እናምናለን" ያሉት ለዚህ ነው። ከላይ እንደ ተገለጸው ሕፃናትም እንዲጠመቁ የሚደረገው ጥምቀት ለድኅነት ወሳኝ ስለ ሆነ ነው። ቅዱስ ጳውሎስም፡- "ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና (በጥምቀት) በመንፈስ ቅዱስ መታደስ አዳነን" በማለት ጥምቀት የመዳን ምሥጢር መሆኑን ጽፎልናል። ቲቶ. 3፡5

እንዲሁም በጥምቀት ዳግም ልደትንና በዚህም የእግዚአብሔር የጸጋ ልጅነትን እናገኛለን። ይህንም ጌታችን "ሰው ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለደ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም" በማለት በማያሻማ ሁኔታ በመለኮታዊ ቃሉ ተናግሯል። ዮሐ 3፡5 በዚህ ልጅነትም ወራሾች እንሆናለን። ሮሜ. 8፡16-17።

ምሥጢረ ሜሮን

ምሥጢረ ሜሮን ለተጠመቁ ሰዎች ከጥምቀት ቀጥሎ ወዲያውኑ የሚፈጸም ምሥጢር ነው። ይህም በቅዱስ ቅባት መቀባትን የሚያመለክት ምሥጢር ሲሆን በዚህም ተጠማቂው በመንፈስ ቅዱስ መታተምንና ሀብታተ መንፈስ ቅዱስን ያገኛል። ሜሮን ለእግዚአብሔር መታተመን ያስገኛል። በዚህ ምሥጢር መፈጸም ተጠማቂው አባቱን እግዚአብሔርንና ፈቃዱን የሚያውቅበትንና ፍቅሩ በውስጡ የሚሣልበትን ጸጋ ያገኛል። ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ስለዚህ ምሥጢርና አገልግሎቱ ሲናገር እንዲህ ይላል፡-

“እናንተም ከቅዱሱ ቅባት ተቀብላችኋል፣ ሁሉንም ታውቃላችሁ። ... እናንተስ ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በእናንተ ይኖራል፣ ማንም ሊያስተምራችሁ አያስፈልጋችሁም። ነገር ግን የእርሱ ቅባት ስለ ሁሉ እንደሚያስተምራችሁ፤ እውነተኛም እንደ ሆነ፣ ውሸትም እንዳልሆነ እናንተንም እንዳስተማራችሁ በእርሱ ኑሩ። 1 ዮሐ. 2:20 ፣ 21 ፣ 27

በአጠቃላይ ይህ ምሥጢር፡- “እንደ ክርስቶስ ስጦታ መጠን ለእያንዳንዳችን ጸጋ ተሰጠን” እንደ ተባለ እያንዳንዱ ይሠራበትና ፈጣሪውን ያገለግልበት ዘንድ እንደየ ዓቅሙ የሚችለውንና የሚጠቅመውን ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታ የሚያገኝበት ምሥጢር ነው። ኤፌ. 4:7 ፣1 ቆሮ. 12:7። ቅዱስ ጳውሎስም ስለዚህ ምሥጢር፡- “ለቤዛ ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ” አለ። ኤፌ. 4:4

ምሥጢረ ቁርባን

ሰው መጀመሪያ ከፈጣሪው ጋር የተጣላው “አትብላ” የተባለውን በመብላቱ ስለ ሆነ ጥንት በመብል ምክንያት የሞተውን ሰው ድኅነቱ ፍጹም ይሆን ዘንድ ዳግመኛ በመብል እንዲድን አደረገው። “አትብላ” የሚለውን “ብላ” በሚል ለወጠለት። እንዲበላ የተሰጠውም እጅግ በጣም የከበረና ስለ ገናናነቱ የሰው አንደበት ሊገልጸው የማይችለው የክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ነው። ለቸርነቱ ወሰን የሌለው እግዚአብሔር እንዲህ አደረገልን። ስሙ ለዘለዓለም የተመሰገነ ይሁን! አሜን።

አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለሙ ሁሉ ቤዛ ይሆን ዘንድ የተወደደ መሥዋዕት አድርጎ ያቀረበው ራሱን ነው። በምሴተ ሐሙስ ፍሥሐ ኦሪቱን ከበሉ በኋላ በዚያው በአንድ ጠረጴዛ ላይ የኦሪቱን መሥዋዕት በአዲስ ለወጠው። ለደቀ መዛሙርቱም እንዲህ አላቸው፡-

“ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ ባረከ፣ ቆርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና፡- እንካችሁ ብሉ፤ ይህ ሥጋዬ ነው አለ። ጽዋንም አንሥቶ አመስግኖ ሰጣቸው፤ እንዲህም

አለ፡- ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ፤ ስለ ብዙዎችም ኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው።” ማቴ. 26:26-28

ስለሆነም ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን የሰጠን ለሁላችንም የኃጢአት ይቅርታ ነው። የኃጢአት ሥርየት ለማግኘት መከፈል የሚኖርበት ዕዳ አለ። ሰው ላጠፋው ጥፋት ራሱ መክፈል ያልቻለውን የኃጢአት ዕዳ ጌታችን በተዋሐደው ሥጋ ራሱ ዕዳችንን በመክፈል ነፃ አወጣን፣ ሥርየትን ሰጠን። ይህን ሥርየት ለማግኘት ስለ እኛ ኃጢአት የተሠዋውን መሥዋዕት መብላትና መጠጣት ይገባል። ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ “ወደሙ ለኢየሱስ ክርስቶስ ያንጽሐነ እምኵሉ ኃጣውኢነ - የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል” ያለው ለዚህ ነው። 1 ዮሐ. 1፡7

ጊዜያዊና ሥጋዊ ምግብን ፈልገው ሲከተሉት ለነበሩት አይሁድ መድኃኔ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ድካማቸው፣ እንዲሁም ምሳሌነቱን ያስረዳቸው ዘንድ ኅብስት አበርክቶ ካበላቸው በኋላ እነርሱ ግን ሰማያዊ ነገርን የማይፈልጉና ሳይሠሩ እንዲሁ በተአምር የሚገኝ ኅብስትን እየተመገቡ መኖር የሚፈለጉ ሆነው ስለ ተገኙ እንዲህ አላቸው፡-

“እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ የምትፈልጉኝ እንጀራን ስለ

በላችሁና ስለ ጠገባችሁ ነው እንጂ ምልክቶችን ስላያችሁ አይደለም። ለሚጠፋ መብል አትሥሩ፤ ነገር ግን ለዘለዓለም ሕይወት ለሚኖር መብል የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ ሥሩ ... የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም፤ በእኔ የሚያምንም ሁል ጊዜ ከቶ አይጠማም። ... የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ። አባቶቻችሁ በምድረ በዳ መና በሉ፣ ሞቱም፣ ሰው ከእርሱ በልቶ እንዳይሞት ከሰማይ አሁን የወረደ እንጀራ ይህ ነው። ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፤ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘለዓም ይኖራል። እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው።” ዮሐ. 6:26-27 ፣ 35:49-51

አይሁድ ይህን ትምህርት ሲሰሙ በማመን ፈንታ “እንግዲህ ይህ ሰው ሥጋውን ልንበላ ይሰጠን ዘንድ እንዴት ይችላል?” በሚል ሥጋዊ አስተሳሰብ እርስ በርሳቸው ተከራከሩ። ጌታችንም ይህን ታላቅና ረቂቅ ምሥጢር በተመለከተ ትምህርቱን በመቀጠል እንዲህ አለ፡-

“እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ የወልደ እጓለ እመሕያው የክርስቶስን ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም። ሥጋዬን የሚበላ ደሜን የሚጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው፤ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ። ሥጋዬ እውነተኛ

መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና። ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል፤ እኔም በእርሱ እኖራለሁ።" ዮሐ. 6:53-58

ኢየሱስ ክርስቶስ የራሱን ሥጋና ደም መብልና መጠጥ አድርጎ ለዓለሙ (ለሰው) ሁሉ ሰጥቷል። ከዚህ የበለጠ ፍቅርና የፍቅር መግለጫ የት ይገኛል? ምንስ አለ? ሰው ሰውን ቢወደውና ደግ ቢሆን ከራሱ ውጭ ያለ ነገርን ያደርግለታል እንጂ ራሱን መብልና መጠጥ አድርጎ ይሰጠዋልን? ጌታችን በግልጽና በአጽንኦት ደጋግሞ እንዳስተማረው የእርሱ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም የዘለዓለም ሕይወትን የምናገኝበትና ከእርሱ ጋር ተዋሕደን የምንኖርበት የሕይወት ምግብ ነው። እንዲሁም ሥጋውን ስንበላና ደሙን ስንጠጣ በመስቀል ላይ ስለ እኛ የተቀበለውን መከራ፣ ሕማሙንና ሞቱን፤ ትንሣኤውንና ዕርገቱን በአጠቃላይ ለእኛ ሲል ያደረገውን ቸርነትና የደረሰበትን መከራ ሁሉ እናስታውሳለን። 1 ቆሮ. 11:26። ስለዚህ ይህን በቸርነቱ የሰጠንን አማናዊ የሕይወት ምግብ እየተዘጋጀን መመገብ ይገባናል። አስቀድሞ "አትብሉ" ተብለን ሳለ በልተን ሞትን፣ አሁን ደግሞ "ብሉ" ስንባል አንበላም ብለን ብንሞት ሁል ጊዜ የተባለውን ትቶ ያልተባለውን ማድረግና ዓመፀኛነት ይሆንብናል።

ይህንም አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ንስሐ እየገባን ስለ ኃጢአታችን ዕለት ዕለት የሚሠዋውን የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋ ክቡር ደም መቀበል ይገባል። ምሳሌው የነበረውን መና እስራኤላውያን በምድረ በዳ ሳሉ አርባ ዓመት ሙሉ ሕፃናትም፣ አዋቂዎችም፣ ሴቶችም፤ ወንዶችም - ሁሉም - በየዕለቱ ሲመገቡ እንደ ኖሩ ሁሉ አማናዊ የሆነውን የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደምም የዕድሜና ሌላ ልዩነት ሳይኖር ሁሉም አንድ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በዚህ ዓለም ሕይወት እስካሉ ድረስ መቀበል ይገባል። ኃጢአትን ለማሸነፍ ኃይልን፣ መንገድ በሆነ በዚህ ዓለም ውጣ ውረድ ደክመን እንዳንዝል ጽናትን የምናገኘው በዚህ ነውና። 1 ቆሮ. 10:3

እነዚህን ምሥጢራት ማለትም ምሥጢረ ጥምቀትን፣ ምሥጢረ ሜሮንን እና ምሥጢረ ቁርባንን ያልፈጸመ ድኅነት የለውም። ከዚህ በኋላ ባለው ሕይወት ለሚገጥሙ ውጣ ውረዶች ደግሞ ምሥጢረ ንስሐ አስፈላጊ ነው። ጥምቀትና ሜሮን የማይደገሙ ሲሆን ምሥጢረ ቁርባን ግን ከላይም እንደ ተገለጸው ሁል ጊዜ ሊፈጸም የሚገባው ነው። ከዚህ በኋላ ባለው ሕይወት ለሚገጥሙ ውጣ ውረዶች ደግሞ በምሥጢረ ንስሐ አማካይነት የሚፈጸሙ ይሆናሉ።

6. ሕጉን መጠበቅ፣ ትእዛዙን መፈጸም፣ ምግባር ትሩፋት መሥራት

አንድ ወጣት ባለጸጋ ወደ ጌታችን ቀርቦ፡- "የዘለዓለምን

ሕይወት እንዳገኝ ምን ላድርግ?" ብሎ ሲጠይቀው ጌታችን "ወደ ሕይወት መግባት ብትወድ ትእዛዛትን ጠብቅ" አለው። ማቴ. 19:16-18 ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት ማመን ብቻ ሳይሆን በተግባርም የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈጸም እንደሚያስፈልግ ሲናገር፡- "በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም" አለ። ማቴ. 7፡21

አንዳንድ ሰዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰኑ ነገሮችን ብቻ ነጥለው በመጠቃቀስ፣ እነርሱ ሊሆን በሚፈልጉት አቅጣጫ በመተርጎምና ሥጋና ደም ያቀበላቸውን በመናገር የሰው ልጅ ለመዳኑ ምንም ዓይነት ድርሻ የለውም፣ ምንም ነገር አይጠበቅበትም የሚል ሃሳብ ያቀርባሉ። ነገር ግን ይህ ሃሳብ ፈጽሞ የተሳሳተ ነው። እነዚህ "በጸጋው ድነናል" እያሉ የሰው ልጅ ለመዳኑ ምንም እንደማይጠበቅበት በማስመሰል ሰዎችን ወደ ሞት ጎዳና የሚመሩ የጥፋት መንገድ ሰባኪዎች ናቸው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ክርስቶስ በተቀበለው መከራና ባደረገው የማዳን ሥራ ድነናልና ከእኛ የሚጠበቅ ምንም ነገር የለም፣ ምግባር ትሩፋት መሥራት አያስፈልገንም" የሚል የተሳሳተ አመለካከት ለነበራቸውና ለሚኖራቸው ሰዎች ሲጽፍ፡- "ነገር ግን በክርስቶስ ልንጸድቅ የምንፈልግ ስንሆን ራሳችን ደግሞ ኃጢአተኞች ሆነን ከተገኘን፤ እንግዲያስ ክርስቶስ የኃጢአት አገልጋይ ነዋ!" በማለት "በጸጋው ሰለ ዳንን ምግባር አያስፈለግም" ማለትና በኃጢአት መኖር ክርስቶስን የኃጢአት አገልጋይ ማድረግ መሆኑን ገልጾአል። ገላ. 2፡17

ለመዳን ከእምነት እና ምሥጢራትን ከመፈጸም ጋር ኃጢአትን መቃወምና ደምን እስከ ማፍሰስ ድረስ መጋደል ያስፈልጋል። ዕብ. 12:4 ለዚህ ነው "በፍርሀትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ" የተባለው። ፊል. 2:12። የክርስትና ጥሪ ለማመን ብቻ ሳይሆን መስቀሉን ለመሸከምና መከራ ለመቀበልም ነው። ፊል. 1:29። ጌታችን መከራ የተቀበለው እኛም የእርሱን አርአያ እንድንከተል ነውና፤ "የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና፤ ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሏልና" እንዳለ። 1 ጴጥ. 2:21። መልካም ምግባር ካልተጨመረበት ከኃጢአት መለየትና መራቅ ብቻም አይበቃም፤ "ተገሐሥ እምኩይ - ከክፍ ሽሽ" ካለ በኋላ "ወግበር ሠናየ - መልካምንም አድርግ፤ ወትነብር ለዓለመ ዓለም - ለዘለዓምም ትኖራለህ" ይላልና። መዝ. 36:27

ጌታችን ስለ ፍርድ ቀን ሁኔታ ሲናገር በቀኙ የሚቆሙትን ዘለዓለማዊ መንግሥቱን ሲያወርሳቸው "ተርቤ አብልታችሁኛልና፣ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፣ እንግዳ ሆኜ ብመጣ ተቀብላችሁኛልና፣ ታርዤ አልብሳችሁኛልና"

በማለት መልካም ሥራቸውን መስክሮ ነው። በግራው የሚቆሙትን ደግሞ “እናንት ርጉማን፣ ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘለዓለም እሳት ከእኔ ሂዱ” የሚላቸው “ተርቤ አላበላችሁኝምና፣ ተጠምቼ አላጠጣችሁኝምና፣ እንግዳ ሆኜ አልተቀበላችሁኝምና፣ ታርዤ አላለበሳችሁኝምና፣ ታምሜ ታስሬም አልጠየቃችሁኝምና” ብሎ ከወቀሳቸው በኋላ ነው። ማቴ. 25:34-36 በዚህ ዓለም ሕይወት ሳሉ ያደረጉት ድርጊት በቀኙ ወይም በግራው ለመቆም እና ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት ወይም ወደ ዘለዓለማዊ ቅጣት የሚሄዱበትን ወሰነ ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ለመዳን መልካም ሥራ አስፈላጊ መሆኑን እንዲህ በግልጽ እየተናገረ ከዚህ በተቃራኒ የሚያስተምሩ መናፍቃንን የሚሰማና በእነርሱ የሚሳሳት ጆሮ ምክንያት የለውም።

በአጠቃላይ ከክርስቲያናዊ ምግባር ርቀው በንስሐ መመለስን እንቢ ብለው በኃጢአት ወድቀውና ጸንተው የሚኖሩ ሰዎች ከእግዚአብሔር መንግሥት ውጭ አንደ ሆኑ ሐዋርያው ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በጻፈው መልእክቱ እንዲህ ሲል አብራርቷል፦

“ወይስ ዓመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳይወርሱ አታውቁምን? አትሳቱ፤ ሴሰኞች ቢሆኑ ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀላጮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠሩ ወይም ሌቦች ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም የሚሰክሩ ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።” 1 ቆሮ. 6:9-10

ለመዳን ሃይማኖትና ምግባር የማይነጣጠሉ መሆናቸውን ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ በመልእክቱ በግልፅ ጽፏል፦
ወንድሞቼ ሆይ፣ እምነት አለኝ የሚል፣ ሥራ ግን የሌለው ሰው ቢኖር ምን ይጠቅመዋል? እምነቱስ ሊያድነው ይችላልን? ... እምነት ከሥራ ተለይቶ የሞተ መሆኑን ልታውቅ ትወዳለህን? አባታችን አብርሃም ልጁን ይስሐቅን በመሠዊያው ባቀረበ ጊዜ በሥራ የጸደቀ አልነበረምን? እምነት ከሥራው ጋር አብሮ ያደርግ እንደ ነበረ፣ በሥራም እምነት እንደ ተፈጸመ ትመለከታለህን? መጽሐፍም፦ አብርሃም እግዚአብሔርን አመነ፣ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት ያለው ተፈጸመ፤ የእግዚአብሔርም ወዳጅ ተባለ። ሰው በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥራ እንዲጸድቅ ታያላችሁ። እንደዚሁም ጋለሞታይቱ ረዓብ ደግሞ መልእክተኞቹን ተቀብላ በሌላ መንገድ በሰደደቻቸው ጊዜ በሥራ አልጸደቀችምን? ::$ Á°. 2፡ 14-26::

የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ የሚያምን ሰው ሕይወቱ ከሚያምነው ጋር የሚስማማና እምነቱን በተግባር የሚመሰክር ሊሆን ይገባዋል። 1 ዮሐ. 2:6 ሰዎችን

የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ የተገለጠው በኃጢአት ለመኖር ሳይሆን ኃጢአትን ድል ለማድረግና ጽድቅን ለመሥራት ነውና፤ ሐዋርያው እንዲህ ሲል እንደ ገለጸው፡-

“ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጧልና፤ ይህም ጸጋ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊ ምኞትን ክደን የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን፤ ራሳችንን በመግዛት በጽድቅ እግዚአብሔርን በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል፤ መድኃኒታችንም ከዓመፅ ሁሉ እንዲቤዠን፤ መልካምንም ለማድረግ የሚቀናውን ገንዘቡም የሚሆነውን ሕዝብ ለራሱ እንዲያነጻ ስለ እኛ ነፍሱን ሰጥቷል፡፡” ቲቶ. 2:11-14

መንፈሳዊ ተጋድሎ ራስን ለመግዛትና በፈቃደ እግዚአብሔር ለመኖር የሚደረግ ጥረትና ውጣ ውረድ በመሆኑ በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ ከፍተኛውን ቦታ ይዞ ይገኛል፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ “የዲያብሎስ ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ፣ መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና” እንዳለ XNÄl MXmÂN እንደ አእምሯቸው ስፋትና እንደ እምነታቸው ጥልቀት በየዓቅማቸው በመልካም ምግባር ተሰማርተው የመልካም ነገር ጠላት ከሆነው ከዲያሎስ ጋር እየታገሉ በተጋድሎ ይኖራሉ፡፡ ኤፌ. 6Ý10(12

ምናልባት መንፈሳዊ ተጋድሎ መጋደል የተሳናቸውና በስም ክርስቲያን ቢባሉም በተግባር ግን የአሕዛብ ዓይነት ሕይወት መኖር የሚሹ ወገኖች ራሳቸውን በማታለያ መጋረጃ ሸፍነው “ድኅነት በጸጋ እንጂ በተጋድሎ አይደለም” በማለት ሰንፈው ለማሳነፍ መንፈሳዊ ተጋድሎን የሚነቅፉ አሉ፡፡ ነገር ግን ይኽ የዲያብሎስ ግብረ አበርነት የሞት መሪነት ነው እንጂ ማንንም የሚጠቅም አይደለም፡፡ ምንም እንኳ ዐቅማችን እየደከመ ሰማያዊነታችንን እየዘነጋን ምድራዊነታችን እየሳበን ብንቸገርም የእያንዳንዳችንን ጥረትና ፍላጎት ደኅና አድርጎ የሚያውቅ እርሱ የቸርነትና የምሕረት እጆቹን እንዲዘረጋልንና ብርታትንና ድል መንሣትን እንዲሰጠን መማጸኑ ከሁሉም የተሻለ ነው፡፡ መዳን እንዲሁ በማመን ብቻ የሚገኝ ቢሆንማ ኖሮ ሐዋርያው “እስመ በብዙኅ ጻማ ወሕማም ሀለወነ ንባእ ለመንግሥተ እግዚአብሔር - ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ ድካምና መከራ እንገባ ዘንድ አለን” ለምን ይል ነበር? የሐዋ፣ 14:22 ወደ ሕይወት የሚወስደውን መንገድ ቀጭን ደጁንም ጠባብ ያሰኘው በክርስትና ሕይወት ውስጥ ጽኑ መንፈሳዊ ተጋድሎ በማስፈለጉ አይደለምን? ማቴ. 7:13-14 በመሆኑም የሰው ልጅ ይድን ዘንድ ሥጋውን የሚጎስምባቸውና ራሱን

የሰው ልጅ ይድን ዘንድ ሥጋውን የሚጎስምባቸውና ራሱን ለፈቃደ እግዚአብሔር የሚያስገዛባቸው መንፈሳዊ ተጋድሎዎች - ጾም፣ ጸሎት፣ ስግደት፣ ዐቂበ ሕዋሳት፣ ምጽዋት፣ ትዕግሥት፣ ትሕትና . . . ያስፈልጉታል።

"እግዚአብሔር ዓለምን ሁሉ አድኗል" ማለት ዕዳችን ተከፍሏል፣ የድኅነት መንገዱ ተከፍቷል ማለት ነው። በዚህ ነገር እሺ ብሎ ለመጠቀም አለዚያም እምቢ ብሎ ለመጎዳት ለእያንዳንዱ ሰው ነጻ ፈቃድ ተሰጥቶታል። እግዚአብሔር ሰውን ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት ይገባ ዘንድ በፍቅሩ ይጠራዋል፣ ይመራዋል፣ የተለያየ የቸርነት ሥራውን ይሠራለታል እንጂ ሰውዬው ሳይፈልግ በግድ ጎትቶ አያመጣውም። ይህም "ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ" ባለው ቅዱስ ቃሉ ግልጽ ሆኖ ይታያል። ዮሐ. 14፡15 ማንም ሰው ትእዛዙን ጠብቆ የመጠቀም፣ ያልፈለገ ደግሞ ባለመጠበቅ ሊጎዳ ነጻ ፈቃድና ሙሉ መብት አለው። ጌታችን አልዓዛርን ከመቃብር ሲያስነሣ የመቃብሩን ድንጋይ ሰዎች እንዲያሡ ሲያደርግ እርሱ ደግሞ ከሞተ አራት ቀን የሆነውን ጠርቶ አስነሣው። ይህን ማድረጉ ሰው በድኅነቱ ላይ የራሱ የሆነ ድርሻ እንዳው ለማሳየት ነው። ዮሐ. 11፡ 39-44

የእያንዳንዱ ሰው ድኅነት በራሱ ላይ የተመሠረተስለ መሆኑ

ምንም እንኳ ሰውን የሚያጸድቀው የእግዚአብሔር ቸርነት እንጂ የእርሱ ሥራ በራሱ ባይሆንም በእግዚአብሔር ቸርነት ለመጠቀምም ቢሆን ከሰው የሚጠበቅ ነገር መኖሩን አይተናል። ኃጥአን የሚፈረድባቸው የእግዚአብሔርን ቸርነት ለመጠቀም የሚያስችል ሥራ ስላልሠሩና በዓመፀ ስለኖሩ ነው እንጂ እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ስለሚጨክን አይደለም። አንድ ሰው ለዘለዓለም ሕይወት የሚበቃውም ሆነ የሚፈረድበት በራሱ ሥራ እንጂ በትውልድ ሐረግ ወይንም በሌላ ሰው ሥራ አይደለም። ሕዝ. 18:20።

ይህን በግልጽ ሲናገር ነቢዩ ዳዊት "እስመ አንተ ትፈድዮ ለኩሉ በከመ ምግባሩ - አንተ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ዋጋውን ትከፍለዋለህ" ይላል። መዝ. 61:12 መድኃኒታችንም "መልካም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና" አለ። ዮሐ. 5:29 እንዲሁም "የሰው ልጅ ከመላእክቱ ጋር በአባቱ ክብር ይመጣ ዘንድ አለውና፤ ያን ጊዜም ለሁሉ እንደ ሥራው ያስረክበዋል" በማለት እያንዳንዱ ሰው በፍርድ ቀን ተነሥቶ የሠራውን ዋጋ እንደሚቀበል ተናገረ። ማቴ. 16:27። ቅዱስ ጳውሎስም ለሮሜ ክርስቲያኖች ይህንኑ ጉዳይ ሰፋ አድርጎ ጻፈ፣ እንዲህ ሲል፦

"እርሱ ለእያንዳንዱ እንድ ሥራው ያስረክበዋል፤ በበጎ ሥራ በመጽናት ምስጋናንና ክብርን የማይጠፋንም ሕይወት ለሚፈልጉ የዘለዓለምን ሕይወት ይሰጣቸዋል፤ ለዓመፃ በሚታዘዙ እንጂ ለእውነት በማይታዘዙትና በአድመኞች ላይ ግን ቁጣና መቅሠፍት ይሆንባቸዋል። ክፉውን በሚያደርግ ሰው ነፍስ ሁሉ መከራና ጭንቀት ይሆንበታል።" ሮሜ. 2.6-9።

እንዲሁም:-
"ሁላችን በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት እንቆማለንና .... እያንዳንዳችን ስለራሳችን ለእግዚአብሔር መለስ እንሰጣለን። ይላል። ሮሜ. 14:10 ፣ 12

ከልባሞቹ ጋር የነበሩት አምስቱ ሰነፎች ደናግል ሙሽራውን ለመቀበል የያዙት መብራት የማይበቃቸው መሆኑን በተረዱ ጊዜ ከልባሞቹ ደናግል ዘይት ለመነ። "ሰነፎቹም ልባሞቹን:- መብራታችን ሊጠፋብን ነው፤ ከዘይታችሁ ስጡን አሏቸው። ልባሞቹ ግን መልሰው:- ምናልባት ለእኛና ለእናንተ ባይበቃስ? ይልቅስ ወደሚሸጥበት ሄዳችሁ ለራሳችሁ ግዙ አሏቸው።" ማቴ. 25:8-9። ሰነፎቹ ከልባሞቹ ዘይት ቢለምኑም ማግኘት ግን አልቻሉም፤ ይልቁንም ሄደው እንዲገዙ ነገሯቸው። ይህ የሚያስረዳው ማንም ሰው ቢሆን የራሱ መብራትና ዘይት (ምግባርና ሃይማኖት) ሙሽራውን ክርስቶስን ለመቀበል የማያበቃው ከሆነ የሌላ የማንም ጽድቅ

ሊረዳው እንደማይችል ነው።

እያንዳንዱ ሰው ተጠያቂ የሚሆነው ለራሱና በራሱ ሥራ ብቻ እንጂ በሌላው ሥራ አይጠየቅም፤ በሌላው ሥራም አይጸድቅም፤ አይኰነንምም። መንፈሳዊ በረከት የሚወረሰውና የሚሰጠው በሥጋዊ ትውልድ ቅርበት ሳይሆን በመንፈሳዊ ሕይወት መሠረት ነው። ከነዓን ምንም እንኳ የታላቁ ጻድቅ የኖኅ የልጅ ልጅ ቢሆንም ኖኅን በማሳዘኑ ከመረገም አላመለጠም። ዔሳው የታላቁ አባት የይስሐቅ የበኩር ልጅ ቢሆንም ብኩርናውን ስላቃለለና ስለ ሸጠ ለአባቱ በረከትና ምርቃት አልታደለም። ሊቀ ነቢያት ሙሴ ጌርሳምና አልዓዛር የተባሉ ሁለት ልጆች ነበሩት። ነገር ግን እስራኤላውያንን መርቶ ምድረ ርስትን የማውረሱን ኃላፊነት የሰጠው ለልጆቹ ሳይሆን ከእርሱ ሳይለይ ከልጅነቱ ጀምሮ እየታዘዘውና እያገለገለው ለኖረው በሥጋ ሳይሆን በመንፈስ ልጁ ለሆነው ለነዌ ልጅ ለኢያሱ ነው። ዘጸ. 33:11

የሊቀ ካህናት የአሮን ልጆች ናዳብና አብዩድ ለክህነት የተመረጡ የነበረ ቢሆንም እግዚአብሔር ያላዘዘውን ሌላ እሳት ባቀረቡ ጊዜ እሳት ወጥቶ እንዳይበላቸው ያዳናቸው ነገር አልነበረም። ዘሌ. 10:1-2 ሕዝበ አይሁድም የአበውን ቃል ኪዳን ሕግና ሥርዓት መሰጠታቸው፣ ወልድየ ዘበኩርየ - የበኩር ልጆቼ -

መባላቸው ሕጉን ባፈረሱ ጊዜ ከቅጣትና ከመከራ ነፃ አላደረጋቸውም። ይሁዳ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ገብቶ መቆጠሩ፣ ሙት ለማንሣት፣ ድውይ ለመፈወስ ሥልጣንን መቀበሉ ክርስቶስን በካደ ጊዜ ምንም አልጠቀመውም።

በሌላ አንጻር ደግሞ ሩት በትውልዷ ከአሕዛብ ወገን ብትሆንም አገሯንና ሕዝቧን፤ ወገኗንና ቤተ ሰዎቿን ሁሉ ትታ የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን በፈለገች ጊዜ ትውልዷ ከአሕዛብ መሆኑ ከክርስቶስ የዘር ሐረግ ገብታ ለመቆጠር አልከለከላትም። ራኬብ አገሯና ሕዝቧ በኃጢአታቸው ሲጠፉ እርሷ ግን ለድኅነት ምክንያት የሚሆን ሥራ ስለ ሠራች ከሕዝቧ ተለይታ ዳነች፤ መዳን ብቻ ሳይሆን ከክርስቶስ የዘር ሐረግ ገብታ ለመቆጠር ቻለች። ማቴ. 1:5። ከነናዊቷ ሴት ምንም እንኳ እርሱ ባወቀ እምነቷና ትሕትናዋ እንዲሁም ጥበቧ እንዲገለጽ ስለ ፈለገ እየጮኸች ስትለምነው ዝም ቢላትና "የልጆችን እንጀራ ለውሾች መስጠት አይገባም" ቢላትም እርሷ ግን በጽኑ ሃይማኖት፤ ከልብ በሆነ ትሕትና እና በሚያስደንቅ ጥበብ ጸንታ በመፈለጓ "ልጆች" የተባሉ እስራኤላውያን በስንፍናቸው ያላገኙትን ደገኛውን ተአምራት አግኝታ ሄደች። ማቴ. 15:22-28

ሰነፎች እስራኤላውያን ግን ለውሾች የሚጣለውን ፍርፋሪ እንኳ ሳያገኙ ቀሩ። ከአሕዛብ ወገን የነበረውን ጢሞቴዎስን ቅዱስ ጳውሎስን ከመከተልና የተወደደ

ልጁ ከመሆን የአባቱ ግሪካዊነት ምን አስቀረበት? የሐዋ. 16:1 ከአሕዛብ ወገን በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑትን ከአብርሃም ከይስሐቅና ከያዕቆብ የዘር ሐረግ አለመሆናቸው ምን ጎዳቸው? ስለሆነም እያንዳንዱ በአባቱ ወይም በዘር ሐረጉ ባሉ ጻድቃን ወይንም በሌላው ሥራ የሚጸድቅ ወይንም በዘር ሐረጉ ባሉ ክፉ ሰዎች ሥራ የሚጎዳና የሚኰነን ሳይሆን በራሱ ሥራ ብቻ ለበረከትም ሆነ ለመርገም፣ ለሞትም ሆነ ለሕይወት ይሆናል።

ይህን በተመለከተ ቤተ ክርስቲያንን በትምህርቱ እስከ ዛሬ ድረስ የሚያበራው ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ በማቴዎስ ወንጌል ትርጓሜው ላይ እንዲህ ይላል፡-

"በቅዱስ መጽሐፍ የጌታችን ወንድሞች የተባሉት ከእርሱ ጋር አንድ ላይ ያደጉና ዝምድና ያላቸው ቢሆኑም እንኳ ራሳቸው በምግባርና በትሩፋት ከመጋደላቸው በስተቀር በመቀራረባቸውና በተዘምዷቸው ብቻ ምንም ያላገኙና ያልተጠቀሙ ከሆነ እኛ ጻድቃን ዘመዶችና ወገኖችን ብንጠራና በእነርሱ በመመካት እነርሱ አሉን ብንል ምን ጥቅም እናገኛለን? ነቢዩ "ወንድም ወንድሙን አያድንም፣ ሰውም አያድንም" በማለት ማንም ማንንም ሊያድን እንደማይችል ተናግሯል። መዝ. 48፡7 የራሱ ሕይወት በግዴለሽነትና በከፋ ኃጢአት የተበላሸ ከሆነ ሌላ ጻድቅ ቢጸልይለት እንኳ እግዚአብሔር አይሰማውም።

ሳሙኤልን ለሳኦል አታልቅስለት እንዳለው፤ ኤርምያስንም “አንተም ስለዚህ ሕዝብ አትጸልይ፤ ከመከራቸው የተነሣ ወደ እኔ በጮኹ ጊዜ አልሰማቸውምና ስለ እነርሱም ጩኸትና ልመና አታድርግ” እንዳለው። ኤር. 11:14። እስራኤላውያን ኃጢአታቸው በበዛ ጊዜ እግዚአብሔር ኤርምያስን እንዲህ አለው፡- “ሙሴና ሳሙኤል በፊቴ ቢቆሙም ልቤ ወደዚህ ሕዝብ አያዘነብልም፣ ከፊቴ ጣላቸው ይውጡ” ኤር. 15:1 በኃጢአት ላይድኑ ለታመሙ ሰዎች አብርሃም ቢለምንላቸውም እግዚአብሔር መንገዱን ይሄዳል። ለእኅቱ የሚለምን ቢኖር የማይገባ ሕይወት ካላት ለሙሴ እንዳለው “አባቷ ምራቁን በፊቷ ቢተፋባት እንኳ ሰባት ቀን ታርፍ ዘንድ ይገባት ነበር” ይላል። ዘኁ. 12:14 ስለዚህ እኛ በባዶ ሕይወት ሆነን የድኅነታችንን ተስፋ በሌሎች ላይ አንጣል። የቅዱሳን ምልጃና ጸሎት ታላቅ ኃይልና ጥቅም አለው፤ ሆኖም ግን እኛ ንስሐ ከገባንና ከተስተካከልን ብቻ ነው።”

እግዚአብሔር በአንዱ ጸሎትና ምልጃ፣ እንዲሁም በአባቶች ቃል ኪዳን ለሌላው ምሕረት የሚያደርግ መሆኑ ከላይ በምዕራፍ ሁለት ተገልጾአል። ያ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ይህ የሚሆነው ግን ጸሎት የሚደረግለት ሰው ምሕረት የሚገባው ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው። ምሕረት የሚገባውንና የማይገባውን የሚያውቀው እርሱ እግዚአብሔር ነው። ራሱ እያዘነና እየተጸጸተ
እግዚአብሔር ነው። ራሱ እያዘነና እየተጸጸተ
የእግዚአብሔርን ይቅርታ ደጅ የሚጸና፤ በቅዱሳን ጸሎት የሚማጸንና ራሱ ማድረግ ያለበትን በተቻለው መጠን የሚያደርግን ሰው የሌሎች ጸሎት በተለይም የቅዱሳን ምልጃና ቃል ኪዳን ይረዳዋል። ደገኛው አባቱ ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንደገለጸው የራሱ ሃይማኖትና ምግባር የካደውን ሰው ግን ሌላ ሊወክለውና ሊጠቅመው የሚችል ነገር የለም።

በሉቃስ ወንጌል በምዕራፍ 16 ከቁጥር 19 እስከ ፍጻሜው ታሪኩ የተገለጸው ባለጸጋ አብርሃምን የተለያየ ልመና ቢለምንም አንዱንም ሊያገኝ ያልቻለው በአብርሃም የማማለድ ጸጋና ክብር ለመጠቀም የሚያስችለው ሕይወት ስላልነበረው ነው። በጥፋቱ ለተጸጸተው ለጌራራ ንጉሥ ለአቤሜሌክ በራሱ በእግዚአብሔር፡- “ነቢይ ነውና ስለ አንተ ይጸልያል፣ ትድናለህም” የተባለሉት ታላቁ አባት አብርሃም ለእግዚአብሔር ምሕረት የሚያበቃ ሕይወት ለሌለው ለዚህ ባለጸጋ ግን “ከዚህ ወደ እናንተ ሊያልፉ የሚፈልጉ እንዳይችሉ፣ ወዲያ ያሉ ደግሞ ወደ እኛ እንዳይሻገሩ በእኛና በእናንተ መካከል ታላቅ ገደል ተደርጎአል” በማለት ቁርጡን ነገረው እንጂ ምንም ነገር አልለመነለትም። ሉቃ. 16.26።